"ሃምሳ ዳቦ ከመላስ  አንድ ዳቦ መጉረስ"
ከዳኛቸው ምህረቱ

ትልቅ ትርጉም ያለው፣ የጥንቱ ተምሳሌት፣
ዛሬም ጠቃሚ ነው፣ ለሚጠቀምበት።

ፓርቲ፣ ግንባር፣ ህብረት፣ ቅንጅት መብዛቱ፣
በድርጅት ውህደት፣ አንድነት ማምጣቱ፣
ለዴሞክራሲያዊ፣ ትግልና ሥልቱ፣
ዋልታ ማገሩ ነው፣ ዋናው መሠረቱ።

ምነው የኛስ በዛ፣ ዓላማውን ሳተ፣
አንዱ በሌላው ስር፣ እየተንኳተታ፣
በቀኝም በግራም፣ እየፈተፈተ፣
ድብቅ ዓላማውን፣ በውስጡ ሸፍኖ፣
ከፊት ሲል ልቋጥር፣ ከሁዋላው በትኖ፣
ማን ማንን ይከተል፣ ማን በማን ተማምኖ?
በሰፊው ሕዝብ ስም፣ በችግሩም ብዛት፣
ብዙ ተቋቁሟል፣ ሀገር አቀፍ ሆነ የቋንቋም ድርጅት፣
አንዱ ሲንሸራተት፣ ሌላውም ሲላላ፣
ሁሉም በያለበት፣ እንደ አሸን ሲፈላ፣
ብልጥ እያሸመቀ፣ ያንን የሌላውን ተመልማይ ሲበላ፣
በስንቱ ጎጆ ውስጥ፣ ሕዝቡ ይከፋፈል?
ሰዎች አስቡበት፣ ትግሉ ተበላሽቷል።

በድርጅት ጥላ፣ ሥልጣን የራባችሁ፣
በድርጅቶች ላይ፣ ድርጅት ፈጥራችሁ፣
በድርጅቶች ሥር፣ ድርጅት ፈጥራችሁ፣
ክተት የምትሉን፣ ከቶ እነማናችሁ?!

ብዙ ልምድ ያላቸው፣ በትግል የታወቁ፣
ጫካ ድረስ ሄደው፣ ቀድመው የታጠቁ፣
በሰላምም ቢሆን፣ ትግሉን የመረጡ፣
በወያኔ ዱላ፣ የተቀጠቀጡ፣
ብዙ ድርጅቶች፣ ተርፈዋል፣ ሞልተዋል፣
የድርጅት ጫጩት፣ በነጋ በጠባ ምን ያስፈልፍላል?

የኢትዮጵያን ሕዝብ፣ የራሱ ባለቤት፣ ለማድረግ ከሆነ፣
የሠላም በሠላም፣ የትጥቅም በትጥቁ፣ ምነው አንድ አልሆነ?
አዳዲስ ድርጅት፣ ለመፍጠር ከመጣር፣
ያሉት ድርጅቶች፣ አንድነት ይጠንክር፣
እውነት አቅም ካለን፣ ያንን እናስተባብር፣
ቀጣፊ ይመስል፣ የገበያ ግርግር፣
እዚያ እየቀነሰ፣ እዚህ በመደመር፣

ከሁዋላ ነጥሎ፣ ከፊት መጠማመር፣
ለማንም አይበጅም፣ ካለፈው እንማር።

“ይኼ ዝም ማለት፣ ለበግም አልበጃት፣
ሃምሳ እራሱዋን ሆና፣ አንድ ነብር ፈጃት።"
ይባላል፣
ድርጅቶች ሁሉ፣ በየትም ያላችሁ፣
ከድርጅት ይልቅ፣ ኢትዮጵያን መርጣችሁ፣
ለዘላቂ ዓላማ፣ መርህ ጨብጣችሁ፣
አንድነት ምከሩ፣ ወቅቱን ተረድታችሁ፣
ያለዚያ አትለፍልፉ፣ ማንም አይሰማችሁ፣
አሁንስ ገለማኝ፣ እኔም ጠላሁዋችሁ።